# የግል መገልገያ ዕቃዎች መመሪያ ቁጥር 51/2010

## የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር

7) **"ከስደት ተመላሽ"** ማለት በተለያዩ ምክንያቶች ከኢትዮጵያ ወጥቶ በስደት የኖረና በራሱ ፈቃድ ወይም በመንግስት ስምምነት ያለ ፓስፖርት ወደ ኢትዮጵያ የሚመለስ ወይም በተቀባዩ አገር የጥገኝነት ጥያቄው ተቀባይነት ያላገኘ እና በራሱ ፈቃድ በሊሴ ፖሴ ወይም በነበረበት አገር መንግስት ተገዶ ወደ ኢትዮጵያ የሚመለስ ኢትዮጵያዊ ነው፡፡

8) **"ትምህርት"** ማለት በትምህርት ሚኒስቴር የከፍተኛ ትምህርት ካሪኩለም የሚታቀፍ ወይም የትምህርት ሚኒስቴር የሚቀበለው የመጀመሪያ ዲግሪ ወይም ከመጀመሪያ ዲግሪ በላይ የሆነ ትምህርት ነው፡፡

9) **"ባለስልጣን"** ማለት የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ነዉ፡፡

10) **"ሚኒስቴር"** ማለት የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ነው፡፡

11) **"አዋጅ"** ማለት የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 ነው፡፡

12) በዚህ መመሪያ ጥቅም ላይ የዋሉ ሌሎች ቃላትና ሀረጎች በአዋጁ የተሰጣቸውን ትርጓሜ ይይዛሉ፡፡

3. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ፡-

ማንኛዉም መንገደኛ፣ ተመላሽ ኢትዮጵያዊ ፣ ከስደተኛ ተመላሽ እና በተለያዩ ሙያዎች ኢትዮጵያ ዉስጥ ለማገልገል በህጋዊ መንገድ ተቀጥሮ ወይም በሌላ ህጋዊ ስምምነት ኢትዮጵያ ዉስጥ ለማገልገል በአየር ወይም በየብስ ወደ ኢትዮጵያ የሚገባ ወይም ከኢትዮጵያ የሚወጣ ኢትዮጵያዊ ወይም ትዉልደ ኢትዮጵያዊ ወይም የዉጭ አገር ዜጋ፣ መንግስት በሚያደርገው ልዩ ጥሪ መሰረት የሚመጣ ኢትዮጵያዊ ወይም ትውልደ ኢትዮጵያዊ ወይም የውጭ አገር ዜጋ ፣ ማንኛውም ባለሀብት እንዲሁም አንድ ዓመት እና ከዚያ በላይ በግል ስራ፣ በቅጥር ወይም በትምህርት ውጭ አገር የቆየ ኢትዮጵያዊ ወደ አገር ውስጥ በሚያስገቧቸው ወይም ከአገር በሚያስወጧቸው የግል መገልገያ ዕቃዎች እና ለንግድ የማይውሉ የግል መገልገያ ዕቃዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡



Records & Document ... No. 3

## ክፍል ሁለት

## የግል መገልገያ እቃዎች እና ለንግድ የማይውሉ የግል መገልገያ እቃዎች

4. **የግል መገልገያ እቃ**

1) ማንኛውም መንገደኛ፡-

ሀ. በዚህ መመሪያ አባሪ በተደረገው ሠንጠረዥ "ሀ" ላይ የግል መገልገያ ዕቃ ተብለው በአይነት፣በመጠንና በብዛት ተለይተው የተዘረዘሩትን ዕቃዎች ቀረጥና ታክስ ሳይከፍል ወደ አገር ውስጥ ማስገባት ይችላል፡፡

ለ. በዚህ መመሪያ አባሪ በተደረገው ሠንጠረዥ "መ" ላይ ለንግድ የማይውሉ የግል መገልገያ ዕቃ ተብለው በአይነት፣በመጠንና በብዛት ተለይተው የተዘረዘሩትን ዕቃዎች ቀረጥና ታክስ ከፍሎ ወደ አገር ውስጥ ማስገባት ይችላል፡፡

ሐ. በዚህ መመሪያ አባሪ በተደረገው ሠንጠረዥ "ሐ" ላይ ወጪ የግል መገልገያ ዕቃዎች ተብለው በአይነት፣ በመጠንና በብዛት ተለይተው የተዘረዘሩትን ዕቃዎች ወደ ውጭ አገር ይዞ መውጣት ይችላል፡፡

2) ተመላሽ ኢትዮጵያዊ ፣ በተለያዩ ሙያዎች ኢትዮጵያ ዉስጥ ለማገልገል በህጋዊ መንገድ ተቀጥሮ ወይም በሌላ ህጋዊ ስምምነት ኢትዮጵያ ዉስጥ ለማገልገል የሚመጣ ትዉልደ ኢትዮጵያዊ ወይም የዉጭ አገር ዜጋ፣ መንግስት በሚያደርገው ልዩ ጥሪ የሚመጣ ኢትዮጵያዊ ወይም ትውልደ ኢትዮጵያዊ ወይም የውጭ አገር ዜጋ፣ ማንኛውም ኢትዮጵያ ውስጥ ኢንቨስት ያደረገ ትውልደ ኢትዮጵያዊ ወይም የውጭ ባለሀብት እና አንድ ዓመት እና ከዚያ በላይ በግል ስራ፣ በቅጥር ወይም በትምህርት ውጭ አገር የቆየ ኢትዮጵያዊ፡-

ሀ. በዚህ መመሪያ አባሪ በተደረገው ሠንጠረዥ "ሠ" ላይ የግል መገልገያ ዕቃ ተብለው በአይነት፣በመጠንና በብዛት ተለይተው የተዘረዘሩትን ዕቃዎች ቀረጥና ታክስ ሳይከፍል ወደ አገር ውስጥ ማስገባት ይችላል፡፡

ለ. በዚህ መመሪያ አባሪ በተደረገው ሠንጠረዥ "ረ" ላይ ለንግድ የማይውሉ የግል መገልገያ ዕቃ ተብለው በአይነት፣በመጠንና በብዛት ተለይተው የተዘረዘሩትን ዕቃዎች ቀረጥና ታክስ ከፍሎ ወደ አገር ውስጥ ማስገባት ይችላል፡፡

## ክፍል ሦስት

## ስለማስረጃ አያያዝና አቀራረብ

5. መረጃ ስለመያዝ

ለዚህ መመሪያ አንቀጽ 4 እና 7 አፈጻጸም ባለስልጣኑ የስጋት ስራ አመራርን መሠረት በማድረግ የተሟላ መረጃ በቋሚነት መያዝ አለበት፡፡

6. ስለማስረጃ አቀራረብ

1) ተመላሽ ኢትዮጵያዊ፡-

ሀ/ በውጭ አገር የቆየበትን ጊዜ እና ጠቅሎ ወደ ኢትዮጵያ መመለሱን የሚገልጽ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የተረጋገጠ (Authenticated) የመሸኛ ደብዳቤ ከነበረበት አገር ካለው ወይም የነበረበትን ሀገር ጭምር ከሚያገለግለው የኢትዮጵያ ኤምባሲ ወይም ቆንስላ ወይም ሚሲዮን ማቅረብ አለበት፡፡

ለ/ የኢትዮጵያ ሚሲዮን ከሌለበት አገር የሚመጣ ከሆነ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የመኖሪያ ፈቃዱን እና የሥራ ውሉን ሳያሰርዝ የመጣ መሆኑን በማጣራት በፓስፖርቱ ላይ በተለጠፈው ስቲከር ላይ ተሰርዟል (void) የሚል ማህተም በማድረግ የሚሰጠውን የመሸኛ ደብዳቤ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

2) ከስደት ተመላሽ፡-

ሀ/ ከስደት ተመላሽ በስደት በቆየበት አገር ካለው ወይም በስደት የቆየበትን ሀገር ጭምር ከሚያገለግለው የኢትዮጵያ ኤምባሲ ወይም ቆንስላ ወይም

ሚሲዮን የተሰጠውን መሸኛ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በኩል አረጋግጦ ማቅረብ አለበት፡፡

ለ/ የኢትዮጵያ ኤምባሲ ወይም ቆንስላ ወይም ሚሲዮን ከሌለበት አገር የሚመጣ ከሆነ ከደህንነት፣ ኢሚግሬሽንና የስደተኞች ጉዳይ ባለስልጣን ከስደት ተመላሽ መሆኑን የሚያረጋግጥ ደብዳቤ ማቅረብ አለበት፡፡

ሐ/ በስደተኛነት ቆይቶ በላኪው ሀገር እና በኢትዮጵያ መንግስት መካከል በሚደረግ ስምምነት መሠረት ወደ ኢትዮጵያ የሚመለስ ከስደት ተመላሽ ከደህንነት፣ ኢሚግሬሽንና የስደተኞች ጉዳይ ባለሥልጣን ከስደት ተመላሽ መሆኑን የሚያረጋግጥ ደብዳቤ ማቅረብ አለበት፡፡

3) <u>ባለሀብት</u>

ማንኛውም ኢትዮጵያ ውስጥ ኢንቨስት ያደረገ ትውልደ ኢትዮጵያዊ ወይም የውጭ ባለሀብት፣ ባለሃብት ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ ማስረጃ ከሚመለከተው የኢንቨስትመንት ኮሚሽን/ቢሮ ማቅረብ አለበት፡፡

4) <u>አግባብ ካለው የመንግስት መ/ቤት ወይም ተቋም ጋር በተደረገ ስምምነት መሰረት በኢትዮጵያ ለማገልገል የሚመጣ ባለሙያ</u>፡-

አግባብ ካለው የመንግስት መ/ቤት ወይም ተቋም ጋር በተደረገ ስምምነት መሰረት በኢትዮጵያ ለማገልገል የሚመጣ የውጭ አገር ነዋሪ ኢትዮጵያዊ፣ ትውልደ ኢትዮጵያዊ እና የውጭ አገር ዜጋ ባለሙያ ስምምነቱን ባደረገው የመንግስት መ/ቤት ወይም ተቋም የበላይ ኃላፊ የተፈረመ ደብዳቤ ማቅረብ አለበት፡፡

5) <u>መንግስት በሚያደርገው ልዩ ጥሪ የሚመጣ</u>

መንግስት በሚያደርገው ልዩ ጥሪ መሰረት በኢትዮጵያ ለማገልገል የሚመጣ የውጭ አገር ነዋሪ ኢትዮጵያዊ፣ ትውልደ ኢትዮጵያዊ እና የውጭ አገር ዜጋ ባለሙያ በጥሪው መሰረት ኢትዮጵያን ለማገልገል መምጣቱን የሚያስረዳ ከነበረበት አገር ካለው ወይም የነበረበትን ሀገር ጭምር ከሚያገለግለው

የኢትዮጵያ ኤምባሲ ወይም ቆንስላ ወይም ሚሲዮን የተሰጠ እና በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የተረጋገጠ (Authenticated) ደብዳቤ ማቅረብ አለበት፡፡

6) <u>በግል ሥራ ፣ በቅጥር ወይም በትምህርት ቆይቶ የሚመጣ</u>

በግል ስራ፣ በቅጥር ወይም በትምህርት ውጭ ሀገር ቆይቶ የሚመለስ ኢትዮጵያዊ ከመጣበት አገር ካለው ወይም የመጣበትን ሀገር ጭምር ከሚያገለግለው የኢትዮጵያ ኤምባሲ ወይም ቆንስላ ወይም ሚሲዮን የተሰጠ በዚሁ ሀገር ውስጥ በግል ሥራ፣ በቅጥር ወይም በትምህርት የቆየ መሆኑን የሚያስረዳ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የተረጋገጠ ደብዳቤ ማቅረብ አለበት፡፡

## ክፍል አራት

## ወጥ የታሪፍ መጣኔ አፈፃፀም

7. <u>ወጥ የሆነ የታሪፍ መጣኔ አወሳሰን</u>

1) በዚህ መመሪያ አባሪ በተደረገው ሠንጠረዥ "መ" እና "ረ" መሰረት የሚገቡ ለንግድ የማይወሉ የግል መገልገያ ዕቃዎች ወጥ በሆነ የታሪፍ መጣኔ መሠረት ቀረጥና ታክስ ተከፍሎባቸው ወደ አገር ውስጥ ይገባሉ፡፡

2) ለንግድ የማይውሉ ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ የግል መገልገያ ዕቃዎች የቀረጥ መጣኔ በጉምሩክ ታሪፍ ምዕራፍ 98 መሠረት ይወሰናል፡፡

3) ባለስልጣኑ ከአጠቃላይ የዋጋ አተማመን መርህ ጋር በማጣጣም ለንግድ የማይውሉ የግል መገልገያ ዕቃዎችን ዝርዝር የመነሻ ዋጋ ያዘጋጃል፡፡

8. <u>ወጥ በሆነ የታሪፍ መጣኔ የማይስተናገዱ ዕቃዎች</u>

ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ዕቃዎች ወጥ በሆነ የታሪፍ መጣኔ ሊስተናገዱ አይችሉም፡፡

1) ባለመብቱ ለራሱ እና ለቤተሰቡ ጥቅም ሊያውለው ከሚችለው መጠን በላይ በተደጋጋሚ የሚያመጣቸው በስጋት ስራ አመራር ክትትል የሚያዙ ዕቃዎች፣
2) ለንግድ ሊውሉ የሚችሉ ዕቃዎች፣
3) ለንግድ የማይውሉ ተብሎ በሠንጠረዥ ከተዘረዘረው መጠን ያለፉ ዕቃዎች፣

Ethiopian Revenues and Customs Authority Record & Documentation

## ክፍል አምስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

9. **ገደብ**

   1) በዚህ መመሪያ አባሪ በተደረገው ሠንጠረዥ "ሠ" እና "ረ" የተመለከተ ማንኛውም ባለመብት የሚያስገባውን ዕቃዎች በሙሉ በአንድ ሰነድ አጠቃሎ ወደ ኢትዮጵያ በገባ በስድስት ወር ጊዜ ዉስጥ ማስገባት አለበት፡፡

   2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተ ባለመብት የግል መገልገያ ዕቃዎቹን በአየር መንገድ እና በየብስ አንድ ጊዜ፣ ሆኖም ከሁለቱ የማስጫኛ ዘዴዎች በአንዱ ብቻ መጠቀም ከፈለገ በየብስ ወይም በአየር መንገድ ሁለት ጊዜ ብቻ ማስገባት አለበት፡፡ ሆኖም በዚህ መመሪያ በተፈቀደው መብት ተጠቃሚ ሊሆን የሚችለው ለአንድ ጊዜ ብቻ ነው፡፡

10. **በሠንጠረዥ ውስጥ ያልተካተቱት ዕቃዎች የሚስተናገዱበት አግባብ**

   1) በዚህ መመሪያ አባሪ በተደረገው ሠንጠረዥ ውስጥ ያልተካተቱ ለግል መገልገያነት የሚውሉ ወይም ለንግድ የማይውሉ የግል መገልገያ ዕቃዎች ሲመጡ በልዩ ሁኔታ በባለስልጣኑ ቅርንጫፍ ስራ አስኪያጅ ወይም እርሱ በሚወክለው ስራ ኃላፊ ውሳኔ ይሰጥባቸዋል፡፡

   2) ባለስልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት በልዩ ሁኔታ የተስተናገዱ ዕቃዎችን መግለጫ እና የዋጋ ዝርዝር የያዘ ሪፖርት በየጊዜው ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፡፡

11. **ስለ ዕቃ አፈታተሽ አግባብ**

   1) ባለስልጣኑ በኢንተለጀንስ የሚያደርገው ክትትል እንደተጠበቀ ሆኖ በአንድ ጉዞ ወይም ጭነት በአውሮፕላን በሚመጣ የመንገደኞች ሻንጣ ወይም የመንገደኞች ዕቃ ላይ 3% ብቻ በመውሰድ በስጋት ስራ አመራር መሰረት የጉምሩክ ፍተሻ ይደረጋል፡፡ ባለስልጣኑ ከብሔራዊ የአየር ትራንስፖርት ፋሲሊቴሽን ኮሚቴ ጋር በመመካከር ዝርዝር አፈፃፀሙ የሚመራበት የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፡፡

Ethiopian Revenues and Customs Authority Records & Documentation No. 2

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት በተደነገገዉ መቶኛ ስርዓት ተወስደው የሚፈተሹ ለንግድ የማይውሉ የግል መገልገያ ዕቃዎች በዚህ መመሪያ በክፍል አራት እና ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው ሰንጠረዥ መሰረት ቀረጥና ታክስ ይከፈልባቸዋል፡፡

3) በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 1 የተገለፀው የስጋት ሥራ አመራር የመንገደኞች ዕቃ ፍተሻ ሥርዓት በሌሎች የማጓጓዛ ዘዴዎች በሚመጡ የመንገደኞች ዕቃዎች ላይ ተፈፃሚ አይሆንም፡፡

4) ማንኛውም ባለመብት ከዚህ መመሪያ ጋር አባሪ በተደረገው ሰንጠረዥ ከተፈቀደው መጠን በላይ ዕቃ ያመጣ እንደሆነ የዕቃውን ቀረጥና ታክስ በእጥፍ ይከፍላል፡፡ ሆኖም ቀረጥና ታክሱን መክፈል ያልቻለ እንደሆነ በትርፍነት ያመጣው ዕቃ ውርስ ተደርጎ ለመንግስት ገቢ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ድርጊቱ በተደጋጋሚ የተፈፀመ እንደሆነ አግባብ ባለው የወንጀል ሕግ መሰረት ተጠያቂ እንዲሆን ይደረጋል፡፡

5) ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም "መንገደኛ" በአንቀጽ 4(2) የተጠቀሱትን ባለመብቶች ይጨምራል፡፡

## 13 <u>የተሻረ መመሪያ ወይም አሰራር</u>

1) ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ፣ አሰራርና ልማድ በዚህ መመሪያ ላይ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

2) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ቢኖርም ይህ መመሪያ በሌላ ሕግ መሰረት የተፈቀደን የግል መገልገያ ዕቃዎች የቀረጥና ታክስ ነፃ መብት አያስቀርም፡፡

## 14. <u>መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ ከታህሳስ 6 ቀን 2010 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ __________ ቀን 2010 ዓ.ም

ዶ/ር አብራሃም ተከስተ
የገንዘብና የኢኮኖሚ ትብብር
ሚኒስትር

| | ሀ | ለ | ሐ | መ | ሠ | ረ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ተ.ቁ | የዕቃው ዓይነት | መለኪያ | ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ የሚፈቀድ የግል መገልገያ ዕቃዎች ብዛት | ለንግድ አላማ የማይውሉ ቀረጥና ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ብዛት | ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ የሚፈቀድ የግል መገልገያ ዕቃዎች ብዛት | ለንግድ አላማ የማይውሉ ቀረጥና ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ብዛት | |
| ተ.ቁ | 5. የሸክላ ዲስክ ማጫዎቻ | መለኪያ | ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ የሚፈቀድ የግል መገልገያ እቃዎች ብዛት | ለንግድ አላማ የማይውሉ ቀረጥና ታክስ የሚከፈልባቸው እቃዎች ብዛት | ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ የሚፈቀድ የግል መገልገያ እቃዎች ብዛት | ለንግድ አላማ የማይውሉ ቀረጥና ታክስ የሚከፈልባቸው እቃዎች ብዛት | |
| 1 | Home Theater with DVD and stand | ሴት | | 1 | 1 | 1 | |
| 2 | Deck with Receiver | ሴት | | 1 | 1 | 1 | |
| 3 | ሬዲዮ/ broadcast reciver | ቁጥር | 1 | 1 | 1 | 2 | |
| 4 | ቴፕ እስከ 2 ካሴት ማጫወቻ | ቁጥር | 1 | 1 | 1 | 1 | |
| 5 | የሆም ሲኒማ ሲስተም ስፒከር | ቁጥር | | 1 | 1 | 1 | |
| 6 | የቴፕ ስፒከር | ሴት | 1 | 1 | 1 | 1 | |
| 7 | የኮምፒዉተር ስፒከር | ሴት | 1 | 1 | 1 | 1 | |
| 8 | ድምፅ ማጉያ(Micro phone) | ቁጥር | | 1 | 1 | 1 | |
| 9 | የሙዚቃ መሣርያ ስታንድ | ቁጥር | | 1 | 1 | 1 | |
| 10 | የቴፕ ካሴት/ሲዲ/ቪዲዮ/ የሸክላ ዲስክ የተለያዩ የተቀረጸበት ያገለገለ | ቁጥር | ነጻ | ነጻ | ነጻ | ነጻ | |

| | ሀ | ለ | ሐ | መ | ሠ | ረ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ተ.ቁ | የዕቃው ዓይነት | መለኪያ | ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ የሚፈቀድ የግል መገልገያ ዕቃዎች ብዛት | ለንግድ ለላማ የማይውሉ ቀረጥና ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ብዛት | ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ የሚፈቀድ የግል መገልገያ ዕቃዎች ብዛት | ለንግድ አላማ የማይውሉ ቀረጥና ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ብዛት | |
| ተ/ቁ | 11. የፀጉር ቤት ዕቃዎችና ተዛማጅ መጠቀሚያዎች | መለኪያ | ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ የሚፈቀድ የግል መገልገያ እቃዎች ብዛት | ለንግድ አላማ የማይውሉ ቀረጥና ታክስ የሚከፈልባቸው እቃዎች ብዛት | ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ የሚፈቀድ የግል መገልገያ እቃዎች ብዛት | ለንግድ አላማ የማይውሉ ቀረጥና ታክስ የሚከፈልባቸው እቃዎች ብዛት | |
| 1 | የፀጉር ቤት ወንበር | ቁጥር | | 1 | 1 | 2 | |
| 2 | የፀጉር ቤት መታጠቢያ ገንዳ | ቁጥር | | 2 | 2 | 2 | |
| 3 | የፀጉር ስታይሰር | ቁጥር | | 2 | 4 | 6 | |
| 4 | ፓይስትራ/ከርለር | ቁጥር | | 2 | 5 | 6 | |
| 5 | የፀጉር ጌጥ | ደርዘን | 2 | 6 | 4 | 6 | |
| 6 | የሰው ፀጉር (Human Hair) | እሽግ | 1 | 2 | 4 | 4 | |
| 7 | ዊግ (አርተፊሻል ፀጉር) | እሽግ | 1 | 2 | 4 | 6 | |
| 8 | ሂና | ደርዘን | 1 | 2 | 2 | 2 | |
| 9 | የፀጉር ቀለም | እሽግ | 1 | 6 | 6 | 12 | |
| 10 | ፐርም | ቁጥር | 2 | 6 | 4 | 6 | |
| 11 | ጄል | ቁጥር | 2 | 6 | 4 | 6 | |
| 12 | የፀጉር ካስክ | በቁጥር | | 1 | 1 | 2 | |

| ተ.ቁ | ሀ<br>የዕቃው ዓይነት | ለ<br>መለኪያ | ሐ<br>ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ የሚፈቀድ የግል መገልገያ ዕቃዎች ብዛት | ነ<br>ለንግድ አላማ የማይውሉ ቀረጥና ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ብዛት | ሠ<br>ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ የሚፈቀድ የግል መገልገያ ዕቃዎች ብዛት | ረ<br>ለንግድ አላማ የማይውሉ ቀረጥና ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ብዛት | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 48 | እንስተኛ ለቤት ውስጥ አገልግሎት የሚውል የእንጨት መላጊያ | ቁጥር | | 1 | 1 | 2 | |
| 49 | እንስተኛ ለቤት ውስጥ አገልግሎት የሚውል የእንጨት ማለስለሻ | ቁጥር | | 1 | 1 | 1 | |
| 50 | ጀነሬተር እስከ 8 ኪሎ wat | ቁጥር | | 1 | 1 | 1 | |
| | **26. ወጪ የግል መገልገያ ዕቃዎች ዝርዝር** | | | | | | |
| 1 | ሽሮ | በኪሎ | 20 | | | | |
| 2 | በርበሬ | በኪሎ | 20 | | | | |
| 3 | ክክ፤ | በኪሎ ግራም | 20 | | | | |
| 4 | ድፍን ምስር፤ አተር፤ ባቄላ፤ ሽምቡራ፤ ቦሎቄ ወዘተ (እያንዳንዱ) | በኪሎ ግራም | 20 | | | | |
| 5 | ሽንኩርት | በኪሎ | 20 | | | | |
| 6 | ዱቄት ( ማንኛውም ዓይነት) | በኪሎ | 30 | | | | |
| 7 | ቆሎ፤ ዳቦቆሎ | በኪሎ | 20 | | | | |
| 8 | የተቆላ ቡና | በኪሎ | 10 | | | | |
| 9 | የተፈጨ ቡና | በኪሎ | 10 | | | | |
| 10 | ጥሬ ቡና | በኪሎ | 10 | | | | |
| 11 | ቅመማቅመም | በኪሎ ግራም | 10 | | | | |
| 12 | ሌሎች | በኪሎ ግራም | 20 | | | | |